## ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

## 4. ምስጢረ-ንሥሓ

- ንስሓ ማለት ቀጥተኛ ትርጉሙ መጸጸት (መመለስ) ማለት ሲሆን ንሥሓ መግባት ማለት በሠሩት ኃጢአት ተጸጽቶ፣ ኃጢትን ለካህን ተናዞ፣ እግዚአብሔርን ምህረት እና ይቅርታ መጠየቅ፣ እንዲሁም ከኃጢአት መንጻት ማለት ነው (ኢዮ 2፣12፤ ማቴ 3፣1፣ ሐዋ 3፣14)፡፡
- በሠሩት ክፉ ሥራ ማዘን ወይም መጸጸት ብቻውን ንሥሓ አይሆንም፡- ‹‹እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ጸጸት የሌለበትን፣ ወደመዳንም የሚያደርሰውን ንሥሓ ያደርጋልና፤ የዓለም ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል›› (1ቆሮ 7፣10)፡፡
    - ጌታውን አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ንዴትና ጸጸት በራሱ ንሥሓ አልሆነውም- (ማቴ 27፣3-6፤ ሐዋ 1፣18-19)፡፡
    - ከዚህም ሌላ ንሥሓ ክፉ ድርጊትን መተው እና የልብ መለወጥን የሚያጠቃልል ነው፡- ‹‹አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ፣ በጾምም፣ በልቅሶና በዋይታ ወደእኔ ተመለሱ፤ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ…›› (ኢዩኤል 2፣12-13፤ ኤር 24፣7)
    - ‹‹ይህን አስቡና አልቅሱ፤ ተላላፊዎች ሆይ ንስሓ ግቡ፤ ልባችሁንም መልሱ›› (ኢሳ 46፣8፤ ሕዝ 18፣30-32)

ምሥጢረ ንሥሓ ‹‹ምሥጢር›› ሊባል የቻለበት ምክንያት ተነሣሒው (ንሥሓ የገባው ሰው) ኃጢአቱ ሲደመሰስ በዓይን ስለማይታይና ረቂቅ ስለሆነ ነው፡፡

### የንሥሓ ጥሪ

- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እና የሐዋርያት ትምህርት ዋና ዓላማም ሰው ሁሉ በንሥሓ እንዲመለስ እና ወደእግዚአብሔር መንግሥት እንዲገባ ‹‹መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች እና ንሥሓ ግቡ›› የሚል ጥሪ (ግብዣ) ነው (ማቴ 3፣1-2፤ 4፣17፤9፣13፤ ዘካርያስ 1፣3…)፡፡
- ምንም እንኳን ክርስቲያኖች በጥምቀት እንደገና (ዳግመኛ) የተወለድን ብንሆንም ሰው ሆኖ ወደኃጢአት ማዘንበል የማይቀር ነውና ጌታችን እንደገና የምንታደስበትን መንገድ ማለትም የንሥሓን ሥርዓት ሰጥቶናል፡፡

- ‹‹… ጌታ ስለተስፋ ቃሉ አይዘገይም፤ ነገር ግን ሁሉ ወደንሥሓ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል›› 1ጴጥ 3፣9፤ 2ጢሞ 2፣25-26

አንድ ሰው ንሥሓ ሲገባ በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል

- ‹‹እኔ ሕያው ነኝ እና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም›› ሕዝ 33፣11

‹‹…ንሥሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንሥሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል›› ሉቃስ 15፣7፤ ማቴ 18፣14

- ‹‹… ንሥሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል›› ሉቃስ 15፣7-10

የምሥጢረ ንሥሓ አፈጻጸም

- አንድ ሰው በሕይት ዘመኑ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊበድል (ኃጢአት ሊሠራ) ስለሚችል ንሥሓ ከሚደገሙ (በተደጋጋሚ ከሚፈጸሙ) ምሥጢራተ ቤ/ክ አንዱ ነው፡፡
- ይሁን እና እግዚአብሔር መሐሪ ነው ብሎ በማሰብ ወይም ንሥሓን ታሳቢ በማድረግ በተደጋጋሚ መበደል ክርስቲያናዊ ጠባይ አይደለም፡፡
- ጌታችን ለሐዋርያቱ ኃጢአትን የማስተስረይ ስልጣን ስለሰጣቸው ተነሣሕያን ንሥሓ መግባት ያለባቸው በካህን (ማለትም በቄስ ወይም በጳጳስ) ፊት በደላቸውን በመናዘዝ (በመንገር) ነው (ዮሐ 20፣21-23፤ ማቴ 16፣19፤ ማቴ 18፣18፤ ማቴ 8፣4)፡፡
  - ‹‹እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታሥሩት ሁሉ በሰማይ የታሠረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል›› ማቴ 18፣18፤ 16፣19
- በብሉይ ኪዳን ሌዋውያን ካህናት የኃጢአት ስርየትን ቢሰጡም ምስጢረ ንሥሓ በዚህ መልኩ አይታወቅም ነበር (ዘሌ 5፣5-19፤ ዘሌ 4፣5-35 ወዘተ)፡፡
- ይህም በመሆኑ ቤ/ክ እያንዳንዱ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲጸና የሚያስተምረው እና የሚያግዘው የራሱ መምህረ ንሥሓ (የንሥሓ አባት) እንዲኖረው ሥርዓት ሠርታለች (ዮሐ 20፣21-23)፡፡

በንሥሐ የሚገኝ መንፋሳዊ ጥቅም

- ንሥሐ በኃጢአት (ባለመታዘዝ) ምክንያት የጠፋን ልጅነት ያስመልሳል፡- ‹‹…ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡ እና አልብሱት፣ ለእጁ ቀለበት፣ ለእግሩም ጫማ ስጡ፤ የሰባውንም ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፤ እንብላም፣ ደስም ይበለን፤ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኗል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቷልም›› ሉቃስ 15፣22-24
- ምህረትን እና ይቅርታን ያሰጣል፡- ‹‹ኃጢአቱን የሚሠውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምህረትን ያገኛል›› (ምሳሌ 28፣13)
    - ‹‹ኑ እንዋቀስ ይላል ግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን፣ እንደአመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች…›› (ኢሳ 1፣18)፡፡
- የተፈጸምን ክህደት እንዳልተፈጸመ ያደርጋል፡- የቅ/ጴጥሮስ ኑዛዜ (ማቴ 26፣ 75…)፡፡
- ዘማዊውን  ዝሙት እንዳልፈጸመ ያደርጋል (2ሳሙኤል 12፣13፤ ዮሐ 8፣11) ፡፡
- የተሰጠን የመንፈሳዊ አገልግሎት ፀጋ እንዳይወሰድብን ያደርጋል፡- ‹‹… እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ  ንሥሐም ግባ፡፡ አለበለዚያ እመጣብሃለሁ፤ ንሥሐም  ባትገባ መቅረዝህን  ከሥፍራው እወስዳለሁ›› ራእይ 2፣5፣16፤ 3፣19)

– ከታዘዘ መቅሰፍት ያድናል፡- ‹‹እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም›› ዮናስ 3፣10

– ከመጨረሻው ፍርድ ያድናል፡- ‹‹…‹ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ› አለው፡፡ ኢየሱስም- ‹እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትሆናለህ› አለው›› ሉቃ 23፣40-43